ውድ ሰራተኞች፣

ስለ እርስዎ **measles, mumps, and rubella (MMR፣ የኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላ)** በሽታ የመከላከል አቅም (መከላከያ) መዝገብ የለንም።

ሁሉም ፈቃድ ያላቸው የህፃናት ማቆያ ማዕከል ሰራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ማቅረብ አለባቸው፡-

1. ቢያንስ አንድ ጊዜ የMMR ክትባት መውሰዳቸውን የሚያሳይ የክትባት መዝገብ።
2. የኩፍኝ በሽታን የመከላከል አቅም እንዳላቸው የሚያሳይ ማረጋገጫ (የደም ምርመራ ወይም ታይተር ተብሎም ይጠራል)።
3. ግለሰቡ በኩፍኝ በሽታ ተይዞ በቂ የሆነ የኩፍኝ መከላከያ አቅም እንዳዳበረ የሚያሳይ ከጤና ባለሙያ የተሰጠ ሰነድ፤ ወይም
4. ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ የተፈረመና በባለሙያው ግምገማ መሰረት የMMR ክትባት ለግለሰቡ የማይመከር መሆኑን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማረጋገጫ።

ለህፃናት ማቆያ ማዕከል ሰራተኞች በግል፣ በፍልስፍና ወይም በሃይማኖታዊ እምነት ምክንያት የMMR ክትባት መሰጠት ከእንግዲህ አይፈቀድም።

በፕሮግራማችን ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ **የኩፍኝ ወረርሽኝ** ከተከሰተ፣ የኩፍኝ በሽታ የመከላከል አቅም ማረጋገጫ ማቅረብ የማይችል ማንኛውም ሰው ለበሽታው ከተጋለጠበት የመጨረሻ ጊዜ ጀምሮ **እስከ 21 ቀናት ድረስ ቤት ውስጥ እንዲቆይ** የጤና ጥበቃ መምሪያ ሊያስገድድ ይችላል። ይህም የኩፍኝ በሽታ ስርጭትን ለማስቆም ይረዳል።

ኩፍኝ በጣም ተላላፊ ነው እንዲሁም በፍጥነት ሊሰራጭ ይችላል። በተጨማሪም ከባድ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎን የWashington State Department of Health (የዋሽንግተን ስቴት የጤና መምሪያን) ይጎብኙ፡- doh.wa.gov/measles።

ስለ ኩፍኝ በሽታ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ከጤና እንክብካቤ ባለሙያዎ ጋር እንዲነጋገሩ እናበረታታዎታለን።

ከሰላምታ ጋር፣